የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

መጋቢት 6/ 2006

## ሕዝብን ለማፋጀት የተነሱትን ማውገዝና ማገድ የዜጋ ግዴታ ነው

የኢትዮጵያን ሕዝብ በሀይማኖትና በብሄረሰብ ከፋፍሎ ሊያጫርስ የተነሰው የለየለት ወያኔ ብቻ ሳይሆን ብሔርተኛ ነን የሚሉ ጠባቦችም ናቸው። በተለይ በምዕራብ ሀገሮች ነዋሪዎች የሆኑ ግለሰቦች ያሉበትን ሀገር መብት በመጠቀም እነዚህ የተለከፉ ግለሰቦች በኢትዮጵያ ላይ የከፈተቱን ጸያፍ ዘመቻ ዜጎች በቸልታ ከቶም ማለፍ የለባቸውም።

የሰብዓዊ መብት ረገጣ ጉዳይ ነውና ሁላችንንም ይመለከታል። ወያኔ እስላም ክርስቲያኑን፤ አማራ ኦሮሞውን ሊያፋጅ የሚካህዲውን ዘመቻ በአሜሪካ ሆነው የሚያጅቡት ብቅ ብቅ ካሉ ቆይተዋል። ይህን ዘመቻ እያጀቡ ካሉት አንዱ ጃዋር መሀመድ የሚባለው ጽንፈኛ ነው። አማራን አረድኩብት የሚለውን ጎራዴ ታጥቆ ፎቶውን ያሰራጨው ይህ ግለሰብ በአማራው ላይ ፍጅትና ጭፍጨፋ ሲጠራ ቆይቷል። በሰሞኑም ቴሌቪዥን ጣቢያ ከፈትኩ የሚለው ይህንኑ ጸረ አማራ ቅስቀሳ በሰፊው ለማስተላለፍ ነው። በማንም ሀገር ቢሆን ሕዝብን ፍጁ፤ እረዱ የሚል የጥላቻ ቅስቀሳ የማስተላለፍ መብት ሊከበር የሚችል አይደለም። ለጃዋር የወጪውን ገንዘብ ማን እንደከፈለለት ባይነገርም ለቃለ መጠቅይ የጋበዘችው ካታርና በጸረ ኢትዮጵያነት የተሰማራችው ግብጽ መጠርጠራቸው አልቀረም። ጃዋር አማራን ግደሉ፤ እረዱ ሲል ቆይቷል። ”ሚኒሊክ ጄኖሳይድ በኦሮሞዎች ላይ” የሚልም ፓል ቶክ ተከፍቶ በ አማራው ላይ ቆሻሻ ዘመቻ ሲያካሂድ ቆይቷል። ወያኔ ራሱ ሙስሊሞ ዜጎችን ሊያፍን ሲፍጨረጨርና፤ ሙስሊምና ክርስቲያኑን ሊያፋጅ ላይ ታች ሲል ባለበትና በአማራው ላይም ሰፊ የጥቃት ዘመቻ በተከፈተብት ጊዜ የነጃዋር አይነቶቹ ሚና የወያኔ ጀሌና ቅጥረኛ መሆን ነው ቢባል ስህተት አይሆንም።

ኢፖእአኮ በሀገራችን የሚፈጸመውን ማንኛውንም የመብት ረገጣ የሚቃውም ነውና ይህን የወያኔንና መሰሎቹን ሕዝብን የሚያፋጅ ዘመቻ በጥብቅ ይቃወማል። በባዕድ ሀገር ነዋሪ ዜጎች ያለባቸውንም ግዴታ አለቸልታ መወጣት አለባቸው ሲልም ያሳስባል። ማለትም --

- ለፓል ቶክ ባለቤቶች የተቃውሞ መልዕክቶች በመላክ ይህን የጽንፈኞች ግደሉ እረዱ ባይ ፓል ቶክ ማሳገድ፤
- የጃዋር ሕዝብን ለፍጅት ዳራጊ የቴለቪዥን ጣቢያ ማስቆም፤
- ጃዋርና መሰሎችን በሕዝብ ፍጅት ቅስቀሳ መክሰስና ለፍርድ ማቅረብ ይጠበቅባችዋል።

መብታችን ሲረገጥ ዝምታ አይበጅም። የአሜሪካም የመጀመሪያ ማሻሻያ ህግ /ፈርስት አሜንድመንት/ የነ ጃዋርን መብት ረጋጭና ሕዝብን ለፍጅት ዳራጊ ልፈፋ አይደግፍም። ጽንፈኛ ክፍሎች ከምዕራብ ሀገሮች ሆነው የሚያሰራጩት ጎጂ ቅስቀሳ (ለምሳሌ በሁቱዎችና ቪአይቶች መሃል) ለስንት እልቂት ሕዝብን እንደዳረገ አይተናል። ለነጃዋር አይነቶቹ ይህን እድል አንስጣቸው።

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE

SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE